| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | የማወራኛ ፡ ዜና ፡፡ |
| ርእስ ፤ | "አቶ ፡ ወሌ ፡ ነጋ ፡ የድል ፡ በዓልን ፡ ፹ኛ ፡ ዓመት ፡ መታሰቢያ ፡ ሰነድያ ፡ በቅርብ ፡ ቀን ፡ እንደሚያግህዱ ፡ አስታወቁ ፡፡ " |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፡፡ |
| ዕለት ፤ | መስከረም ፡ 13 ፡ ቀን ፡ 2014 ፡ ዓ.ም. ፡፡ |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ፡፡ |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፥ ቍ.2014-001 ፡፡ |
| ማስታወሻ ፤ | የድል ፡ በዓል ፡ 80 ኛ ፡ ዓመት ፡ መታሰቢያ ፡፡ |
| ማሳሰቢያ ፤ | መስከረም ፡ 28 ፡ ቀን ፡ 2014 ፡ ዓ.ም. ፡ ተዘምኗል ፡፡ |

# ማወራኛ

media | وَسِيلَة

## አቶ ፡ ወሌ ፡ ነጋ ፡ የድል ፡ በዓልን ፡ ፹ኛ ፡ ዓመት ፡ መታሰቢያ ፡ ሰነድያ ፡ በቅርብ ፡ ቀን ፡ እንደሚያግህዱ ፡ አስታወቁ ፡፡

ኢትዮጵያ ፡ ፋሺስት ፡ ኢጣሊያን ፡ ድል ፡ ያደረገችበትን ፡ 80 ኛ ፡ ዓመት ፡ መታሰቢያ ፡ ለማክበር ፥ የድምፅና ፡ ርእይ ፡ ሰነድያ ፡ (film documentary) ፡ የሚያሰናዱት ፡ አቶ ፡ ወሌ ፡ ነጋ ፥ ሰነድያውን ፡ በቅርቡ ፡ አጠናቀው ፡ ለሕዝብ ፡ እይታ ፡ እንደሚያበቁት ፡ አስታውቀውናል ፡፡

ባደረጉልን ፡ ግብዣ ፡ መሠረት ፥ ቅድመ ፡ ግህደቱን ፡ ለማየት ፡ ታድመንላቸው ፡ ነበር ፤ በሥራውም ፡ እጅግ ፡ ተደስተናል ፡፡

አቶ ፡ ወሌ ፡ ነጋ ፥ በመጋቢት ፡ ወር ፡ 2013 ፡ ዓ.ም. ፡ ባስተላለፉት ፡ ጥሪ ፡ መሠረት ፥ ከ 27 ፡ ያላነሱ ፡ ባለታሪኮች ፣ ባለሚያዎችና ፡ ቤተሰቦች ፡ አስተዋፅኦዎቻቸውን ፡ በታላቅ ፡ ቸርነትና ፡ እምነት ፡ ስላደረሱላቸው ፡ እጅግ ፡ ባለውለታቸው ፡ መኾናቸውንና ፥ ጠቅላላው ፡ ዝግጅት ፡ ኹሉንም ፡ እንደሚያስደስትላቸው ፡ ተስፋቸውን ፡ ገልጸውልናል ፡፡

የሦስት ፡ ሰዓቱ ፡ ሰነድያ ፥ በድምፅና ፡ በርእይ ፡ የተቀናበሩ ፡ ዐያሌ ፡ ታሪካውያን ፡ መረጃዎችን ፡ ይዟል ፡፡ ከዐፄ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ እስከ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፥ ከደጃዝማች ፡ ባልቻ ፡ ሳፎ ፡ እስከ ፡ ራስ ፡ አበበ ፡ አረጋይ ፥ ከራስ ፡ ሙሉጌታ ፡ ይገዙ ፡ እስከ ፡ ራስ ፡ ደስታ ፡ ዳምጠው ፥ ከደጃዝማች ፡ ኀይሉ ፡ ከበደ ፡ እና ፡ ወይዘሮ ፡ ሸዋ ፡ ነሽ ፡ አብርሃ ፡ እስከ ፡ ደጃዝማቾች ፡ ወንድ ፡ ወሰን ፡ ካሳ ፣ አበራ ፡ ካሳ ፣ አስፋ ፡ ወሰን ፡ ካሳ ፥ ከቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ ደምሰው ፡ እስከ ፡ ቢትወደድ ፡ አዳነ ፡ መኰንን ፥ ከደጃዝማች ፡ ኀይሌ ፡ አባ ፡ መርሳ ፡ እስከ ፡ ደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ መሸሻ ፥ ከደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ ጋሪ ፡ እስከ ፡ ደጃዝማች ፡ በቀለ ፡ ወያ ፥ ከደጃዝማች ፡ ዘውዴ ፡ አስፋው ፡ ዳርጌ ፡ እስከ ፡ ሊ. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ከቢትወደድ ፡ ነጋሽ ፡ ወርቅነኽ ፡ እስከ ፡ ደጃዝማች ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፥ ከራስ ፡ ኀይሉ ፡ በለው ፡ እስከ ፡ ደጃዝማች ፡ ዘውዱ ፡ አባ ፡ ኰራን ፥ ከራስ ፡ ውብነኽ ፡ ተሰማ ፡ እስከ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬ ፥ ከልጅ ፡ ኀይለ ፡ ማርያም ፡ ማሞ ፡ እስከ ፡ ከደጃዝማች ፡ ፀሐዩ ፡ ዕንቈ ፡ ሥላሴ ፥ ከደጃዝማች ፡ ዑመር ፡ ሰመተር ፡ እስከ ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ሎሬንሶ ፡ ታእዛዝ ፥ ከደጃዝማች ፡ ኀይለ ፡ የሱስ ፡ ፍላቴ ፡ እስከ ፡ ብሪጋዲየር ፡ ጄኔራል ፡ አበበ ፡ ተፈሪ ፥ ከዘርዓይ ፡ ድረስ ፡ እስከ ፡ ሞገስ ፡ አስገዶም ፥ ከደጃዝማች ፡ ገረሱ ፡ ዱኪ ፡ እስከ ፡ አብዲሳ ፡ አጋ ፥ ከደጃዝማች ፡ ወርቁ ፡ ሥንቁ ፡ እስከ ፡ ባሻ ፡ ወልዴ ፥ ከደጃዝማች ፡ አበበ ፡ ሸንቀጡ ፡ እና ፡ ተሾመ ፡ ሸንቀጡ ፡ እስከ ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደራሴ ፡ ዓለማየኹ ፡ አበበ ፥ ከራስ ፡ መስፍን ፡ ስለሺ ፡ እስከ ፡ ደጃዝማች ፡ ተሰማ ፡ ርገጤ ፥ ከቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡ እስከ ፡ ሊ. ፡ ጄኔራል ፡ ዐቢይ ፡ አበበ ፥ ከደጃዝማች ፡ መሸሻ ፡ ወልዴ ፡ እስከ ፡ ፊታውራሪ ፡ ማሞ ፡ አሸኔ ፥ ከደጃዝማች ፡ ዐባይ ፡ ካሳ ፡ እስከ ፡ ቀኛዝማች ፡ ይብሳ ፡ በሪ ፥ ከደጃዝማች ፡ ሀብተ ፡ ሥላሴ ፡ በላይነኽ ፡ እስከ ፡ ብ. ፡ ጄኔራል ፡ ጃገማ ፡ ኬሎ ፥ ከወይዘሮ ፡ ሸዋ ፡ ረጎድ ፡ ገድሌ ፡ እስከ ፡ ወይዘሮ ፡ ልክ ፡ የለሽ ፡ በያን ፥ ከፊታውራሪ ፡ ተክለ ፡ ሐዋርያት ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፡ እስከ ፡ ጸሓፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ፥ ከአለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ እስከቀኝ ፡ ጌታ ፡ ዮፍታሔ ፡ ንጉሤ ፥ ከጄኔራል ፡ መርዕድ ፡ መንገሻ ፡ እስከ ፡ ሊ. ፡ ጄኔራል ፡ ከበደ ፡ ገብሬ ፥ ከአቶ ፡ ሐዲስ ፡ ዓለማየኹ ፡ እስከ ፡ ሊ. ፡ ጄኔራል ፡ ሙሉጌታ ፡ ቡሊ ፥ ሌሎችም ፡ ስማቸው ፡ ያልተጠራ ፡ ታላላቅ ፡ ሀገራውያን ፡ ዠግኖች ፡ የኢትዮጵያ ፡ የቍርጥ ፡ ቀን ፡ ልጆች ፥ ወታደሮችና ፡ ዐርበኞች ፡ ተዘክረውበታል ፡፡

ሰነድያው ፡ በሚከተሉት ፡ ሦስት ፡ መርበቢያዎች ፡ እንደሚጋድ ፡ ታውቋል ፡—

www.awde-qelem.net

www.gzamargna.net

www.slttunhzb.net

አዘጋጁን ፡ አቶ ፡ ወሌ ፡ ነጋን ፥ ላበረከቱልን ፡ ታሪካዊ ፡ ሥራ ፡ እጅጉን ፡ እናመሰግናለን ፡፡ ሰነድያውን ፡ በማስተዋወቅ ፡ ረገድ ፡ መርበቢያችን ፡ www.slttunhzb.net ፡ እና ፡ "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፡ ሙሉ ፡ ትብብራቸውን ፡ ያደርጉላቸዋል ፨


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2014 ፡ ዓ.ም. ፡፡